**ደቡብ ግሎባል ባንክ**

**Debub Global Bank**

# የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

የደቡብ ግሎባል ባንክ አ.ማ የባለአክሲዮኖች 8ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ታህሳስ 10 ቀን 2013 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ ጊዮን ሆቴል ግቢ ውስጥ በሚገኘው ግሮቭ ጋርደን ዎክ ስለሚካሄድ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክብሮት ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**<u>የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳዎች</u>**

1. የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ፤
2. የአክሲዮን ዝውውሮችና የአዳዲስ አክሲዮኖችን ሽያጭ ማሳወቅ፤
3. የ2019/20 ዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማድመጥ፤
4. 2019/20 የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማድመጥ፤
5. በዳይሬክተሮች ቦርድ እና በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፤
6. የ2019/20 የተጣራ ትርፍ ድልድል ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን አበል መወሰን፤
8. የውጭ ኦዲተሮች መሾምና አበላቸውን መወሰን፤
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ሪፖርት ማድመጥ፤
10. እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ማድረግ፤
11. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ማካሄድ፤
12. የጉባኤውን ቃለጉባኤ ማጽደቅ፤

## ማሳሰቢያ

- ☞ በጉባኤው ላይ በአካል መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ከሕዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 9 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ከኢትዮጵያ ሆቴል በስተጀርባ ናሽናል ታወር ከሚገኘው የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት 9ኛ ፎቅ የሕግ አገልግሎት መምሪያ በመቅረብ የውክልና ቅጽ በመሙላት ወይም አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተረጋገጠ በስብሰባ ለመሳተፍና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ስልጣን ማስረጃ ወይም የሞግዚትነት ማስረጃ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ይዛችሁ በመቅረብ በጉባኤው ላይ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡
- ☞ ባለአክሲዮኖች ሆኑ ወኪሎች ወደ ስብሰባው ስትመጡ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ እንደዚሁም የድርጅት ተወካዮች ሃላፊነታችሁን የሚያሳይ ማስረጃ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን፡፡
- ☞ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከልና ለጋራ ጤንነታችን ሲባል የስብሰባው ተሳታፊዎችን ቁጥር ለመቀነስ ይቻል ዘንድ ባለአክሲዮኖች ውክልና እንድትሰጡ የሚመከር ሲሆን በጉባኤው ላይ የሚገኙ ተሳታፊዎች በሙሉ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል (ማስክ) ማድረግና ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎች መከተል አለባቸው፡፡
- ☞ በዕለቱ ጉባኤው ተወያይቶ የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች በጉባኤው ባልተገኙ አባላት ላይ ጭምር የፀና ይሆናል፡፡

### ደቡብ ግሎባል ባንክ አ.ማ

### የዳይሬክተሮች ቦርድ